# ኒያላ ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር

## የባለአክሲዮኖች 31ኛ ዓመታዊ መደበኛ እና 24ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔዎች ጥሪ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ንግድ ሕግ አንቀጽ 366(1) ፣ 367(1) እና አንቀጽ 370 እንዲሁም በአክሲዮን ማህበሩ መመስረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 16.1 መሠረት የኒያላ ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር የባለአክሲዮኖች 31ኛ ዓመታዊ መደበኛ እና 24ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔዎች ቅዳሜ ታህሳስ 18 ቀን 2018 ዓ.ም. ከጥዋቱ 2:30 ሰዓት ጀምሮ በሸራተን አዲስ ሆቴል ሰሜን የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ይካሄዳሉ፡፡ በመሆኑም የተከበራችሁ የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች በዕለቱ በጉባኤዎቹ ላይ እንድትገኙልን የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

### 1. ማህበሩን የሚመለከቱ ወና ዋና መረጃዎች

1.1 የአክሲዮን ማህበሩ ዋና መ/ቤት አድራሻ ----- አ.አ. ቦሌ ክ/ከ ወረዳ 04፣ የቤ.ቁ. 330፣ ስልክ +251116626667፣ ኢሜል nisco@ethionet.et ድረ-ገጽ www.nyalainsurancesc.com

1.2 የአክሲዮን ማህበሩ የንግድ ዘርፍ --------------------------- ኢንሹራንስ

1.3 የአክሲዮን ማህበሩ የንግድ ምዝገባ ቁጥር ---------------- BL/AA/3/0017533/2011

1.4 የአክሲዮን ማህበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ (ካፒታል) ---- ብር 1,793,309,000.00

1.5 የአክሲዮን ማህበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ (ካፒታል) ------ ብር 1,680,142,000.00

### 2. የ31ኛው የባለአክሲዮኖች ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች

2.1 ምልዓተ-ጉባዔ መሟላቱን ማረጋገጥ፣

2.2 እስከ ጉባዔው ቀን የተፈጸሙትን የአክሲዮን ሽያጮችን እና ዝውውሮችን ማጽደቅና አዳዲስ ባለአክሲዮኖችን መቀበል፣

2.3 የዳይሬክተሮች ቦርድ እ.ኤ.አ. የ2024/25 የሥራ ክንውን ሪፖርት ማድመጥና ተወያይቶ ማጽደቅ፣

2.4 እ.ኤ.አ. የ2024/25 የሥራ ዘመን የውጭ ኦዲተሮችን ሪፖርት ማድመጥና ተወያይቶ ማጽደቅ፣

2.5 እ.ኤ.አ. የ2024/25 የተጣራ ትርፍ አደላደል እና አከፋፈል በዳይሬክተሮች ቦርድ በቀረበ የውሳኔ ሃሳብ ላይ ተወያይቶ መወሰን፤ ክፍያዉ የሚፈጸምበትን ቀን መወሰን፣

2.6 እ.ኤ.አ. ለ2025/26 የሥራ ዘመን የውጭ ኦዲተሮችን መሾምና አበላቸውን መወሰን፣

2.7 ለቦርድ አባላት እ.ኤ.አ. ለ2025/26 ወርሃዊ አበልና ከ2024/25 የተጣራ የትርፍ ድርሻ ላይ የሚታሰብ ክፍያን መወሰን፣

2.8 የቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ አባላትን ወርሃዊ አበል ክፍያን ማጽደቅ፣

2.9 የቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ የሥራ ክንውን ሪፖርትን ማድመጥ እና የቦርድ አባላትን ምርጫ ማካሔድ

## 3. የ24ኛው የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች

3.1 ምልዓተ-ጉባዔ መሟላቱን ማረጋገጥ፤

3.2 ተፈርመው ሙሉ በሙሉ ያልተከፈሉ የኩባንያው አክሲዮኖች ላይ ተወያይቶ መወሰን

3.3 የኩባንያውን ካፒታል ማሳደግ፤

3.4 የአክሲዮን ማህበሩን መመስረቻ ጽሁፍ ማሻሻል

## 4. ማሳሰቢያ፡

4.1 በጉባዔው ላይ መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች ተወካዮቻችሁ ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ የተሰጠ የውክልና ሰነድ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ በመያዝ ወይም በንግድ ሕግ አንቀጽ 377 መሠረት ጉባዔው ከመካሄዱ ከሦስት ቀን በፊት በኒያላ ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር ዋና መ/ቤት፣ 1ኛ ፎቅ፣ ቢሮ ቁጥር 106 በአካል በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ በማህበሩ የተዘጋጀውን የውክልና ቅጽ ሞልተው በመፈረም ተወካይ መሾምና ተወካዩም የውክልና ማስረጃውን በመያዝ የጉባዔው ተካፋይ ለመሆንና ድምጽ ለመስጠት የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡ ሆኖም አንድ ባለአክሲዮን በማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔ በማንኛውም ችሎታ መወከል የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ስለመሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

4.2 የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባዔው ላይ ለመሳተፍ ሲመጡ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፈቃድ ዋናውን እና ኮፒ በመያዝ በጉባዔው ላይ መሳተፍ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ትውልደ ኢትዮጵያዊያን የሆኑ የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ትውልደ ኢትዮጵያዊያን መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ቀኑ ያላለፈበት መታወቂያ (ቢጫ ካርድ) ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

**የኒያላ ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር የዳይሬክተሮች ቦርድ**